የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No. 37
ADDIS ABABA, 15th July, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፰/፪ሺ፲፫

ለኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚ መሠረት የመጣል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …………….ገጽ ፲፫ሺ፬፻፷፰

## Content

Proclamation No. 1258/2021

International Development Association Loan Agreement for financing Ethiopia Digital Foundations Project Ratification Proclamation…….............................Page 13468

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፰/፪ሺ፲፫

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚ መሠረት የመጣል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል አንድ መቶ ሠላሳ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፩፻፴፰ ሚሊዮን ፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ሚያዚያ ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአካሄደው ፭ኛ ልዩ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO 1258/2021

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to One Hundred Thirty-Eight Million Nine Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 138,900,000) for financing Ethiopia Digital Foundations Project, was signed in Addis Ababa on 7th day of May, 2021;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 5th special session held on 7th day of July, 2012;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚ መሠረት የመጣል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማኀበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፰/፳፻፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሚያዚያ ፳፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6856-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አንድ መቶ ሠላሳ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፩፻፴፰ ሚሊዮን ፱፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት**

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Ethiopia Digital Foundations Project Ratification Proclamation No. 1258/2021".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 6856-ET signed in Addis Ababa on 7th day of May, 2021 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to One Hundred Thirty-Eight Million Nine Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 138,900,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 15th Day of July, 2021.**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDNET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**